የካቲት14 ቀን 2001 ዓ.ም

# ምርጫችን ሕዝባችን ልጆቹን የገበረበት የግንቦት 97 ድምፃችን ነው!!

ከአያልነሽ

- ምርጫችን ሕዝባችን የሞተበት፣ ከቤቱ የተፈናቀለበት፣ ቀንበጦችን እነ ሽብሬ ደሳለኝንና ሌሎች ለግላጋ ወጣቶችን የገበርንበት የግንቦት 1997 ዓ.ም ድምፃችን ነው።

- ምርጫችን፥ ሕዝባችን መመረጥ መብትህ ነው ተብሎ፣ መብቱን ተጠቅሞ በሥነ ሥርዓትና በአግባቡ የምርጫ ህጉን አክብሮ ከጥዋት እስከ ማታ ቆሞ ተራውን በመጠበቅ ድምፁን የሰጠበት ድምፃችን ነው።

- ምርጫችን፥ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር ታዛቢ ሆኖ የመሰከረበት፣ ህዝባችን የድምፁን ሳጥን በቀማኛው የወያኔ ቅልብ ላለማስነጠቅ ዘብ ሆኖ የተገደለበት ድምፁ ነው የእኛ ድምፅ።

- ምርጫችን፥ ሕዝባችን በጠመንጃ ከታጠረ የወንበዴ አገዛዝ ጋር ግብግብ ገጥሞ በድምፁ  የጎጥ፣ የጠባብና የመንደር ሽፍታ አይገዛኝም ብሎ እንቢተኝነቱን በመግለጽ፣ የተዋደቀበት ድምፁ ነው ድምፃችን፥

- ምርጫችን፥ በመሣሪያ ኃይል የተዘረፈውን የሕዝባችንን ድምፅ ማስመለስ ነው።

- በአጠቃላይ ምርጫችን የተሠረቀው የሕዝባችን ድምፅ ይከበር፣ይመለስ የሚለው ነው ጭሆታችን።

በቅርቡ በ2002 ኢትዮ.አቆጣ ወይም በ2010 (አውሮ፣አቆጣጠር) ይደረጋል ተብሎ በወንበዴው አገዛዝ ሽርጉድ የሚባልለት ምርጫ  ህዝባችንን በሽብር እየናጠ ነው። በግንቦቱ ምርጫ 1997 ዓ.ም  ሕዝባችን  በመስዋዕትነቱ የሰጣቸውን ድምፅ ሆነ ድል በፈቃዳቸው ያሰረከቡ የትናንትና የምርጫ 97 ተዋናዮች፣ ዛሬ ደግሞ በወያኔ ተከልለው ያፈሩት ንብረታቸውንና ሃብታቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ በጭንቅ ላይ ናቸው። በዚህ የ2002 ምርጫ ድራማ ላይ ለመጨፈር ከወዲያ ወዲህ ሲወራጩ የምንመለከታቸው ግለሰቦች ሆኑ ቡድኖች ዝም ብለው ሳይሆን ከአገዛዙ ጋር የተያያዙበት እትብትና ጥቅም ስላለ ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ እነኝህ ግለሰቦች ሲያሻቸው በግል ሳያስፈልጋቸው ደግሞ ተደራጅተን መጣን በማለት ለ2010ሩ ምርጫ አለን አለን በማለት የሚባክኑት ከ5 ዓመት በፊት ሕዝብን ለሞት፣ ለእስርና፣ ለስደት የዳረገውን የምርጫ 97ን አሰቃቂ ጠባሳ ሳንረሳ ነው፤ በአሁኑ ወቅት በዚያ ምርጫ ጦስ አገርና ሕዝብ እንዳለ ታስሮ ባለበት ሁኔታ (ለእነርሱ ይሄ ጭንቃቸው አይደለምና)፣ እንደገና  ሊበቀል ለተዘጋጀው ወያኔ ሕዝባችንን ሊያስሙቱ ጭራቸውን እየቆሉ በመሆኑ፣ ሕዝባችን ዳግመኛ እንዳይመታ ልንከካል  ይገባል ባይ ነኝ።  ወያኔ ከምርጫ 97 በኋላ እየቀጠለ ያለው በደመ ነፍስና በተናጋ መሬት ላይ ቆሞ እየተንገዳገደ ነው።  ይህ የተናጋ መሬት ደግሞ እንዳይደረመስበት እጅግ ተጠንቅቆ በጭንቅ የሚራመድበት ረግረግ ጭቃ ነው።  በአጭሩ በምላጭ ራስ ላይ እንደመረማመድ ማለት ነው። ይሄ ደግሞ እውነታ እንጅ ፕሮፓጋንዳ አይደለም። በኢትዮጵያችን አሁን መሬት ላይ ያለው ሐቅ ይነገር ከተባለ፣

ከምርጫ 97 በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ተቆጥቶ አሻፈረኝ በማለት በዝምታው አገዛዙን እየስጨነቀና እየገዘገዘ ያለበት ሁኔታ ነው። የወያኔና የሕዝባችን ቅራኔ መሠረታዊ ቅራኔ በመሆኑ መሠረታዊ ለውጥን የሚጠይቅ እንጅ በጥገናዊ ለውጥ የማያገግም ለመሆኑ ፈጦ እየታዬ ነው። ይሄ ደግሞ ፈልግነውም አልፈለግነው የቅራኔው መጦዝ የፈጠረው ውጤት ነው። በሕዝቡና በአገዛዙ መካከል ያለው እውነታ ይሄ ሆኖ ሳለ እንዲያውም ወያኔ በውስጡ አፍኖና ደብቆ ለያዘው የውስጥ ጭንቀቱ ይደብቁለት ዘንድ ወደ ውጭ በበተናቸውና በላካቸው የወያኔ ደንገጡሮች፣ እንደልባቸው እንዲያጭበረብሩና እያምታቱ እንዲቀጥሉ (አውቀንም ሆነ ሳናውቅ) የተመቻቸነው ሀገር ቤት ካለው ሕዝብ ይልቅ፣ በውጭ የምንኖረው ኢትዮጵያዊያን ነን ብል ማጋነን አይሆንም። ከግንቦት 1997 ምርጫ በኋላ፣ ህዝባችን ስለእያንዳንዱ የድርጅት "መሪ ነን ባይ" ማንነትና፣ ስለ ድርጅቶች ምንነትም ከማንም፣ ከምንም በላይ አብጠርጥሮ አውቋል። ማን ከሕዝብ ጋር እንደቆመና ማንስ ከአገዛዙ ጋር በተዘዋዋሪ እጅና ጓንት ሆኖ እያገለገል እንዳለ ከበቂ በላይ መረጃ አለው። ወያኔም ይሄንን ተገንዝቦ የህዝቡን ዝምታ ለመዳሰስ ብዙ ነገሮችን እየሞከረ ይገኛል። ከሞከራቸው ውስጥ በቅርቡ ያደረገው ተከባብሮና ተቻችሎ ለዘመናት አብረው በኖሩ የእስልምናና የክርሥትና ኃይማኖት ተከታዮችን ለማጋጨት የወረወረው አለሎ አንዱ ነው። ደግነቱ ወያኔ በባነነ ቁጥር ሊተኩስ የሚያስበውን ጥይት ከመተኮሱ በፊት ህዝቡ አስቀድሞ ስለሚያውቅ በየቀኑ ለጭንቀቱ መፈተሻ የሚወስዳቸውን የደመነፍስ እርምጃዎች፣ መልሶ ወደራሱ እንዲመለስ በማድረግ ራሱን እየለበለበው በመቸገር ላይ ነው። ወያኔ ሲጨነቅ ደግሞ አብረው የሚከስሉትና ከወያኔ በላይ እጅግ የሚጨነቁት፣ በውጭም ሆነ በሀገር ቤት ያሉ በወያኔ አገዛዝ ጥላ ስር ተጠልለው ኃብት ያፈሩና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሚሊየነር የሆኑት ዋነኞቹ ናቸው። ለምሳሌ እነስዬ አብርሃ፣ ገብሩ ዓስራት፣ ብርሃኑ ነጋ ፣ ብርሃነ መዋ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ጎልተው የሚታዩት አገር ቤት ውስጥ በባለቤቶቻቸውና በቤተሰቦቻቸው ሥር የሚንቀሳቀስና የሚመራ ኃብት ያላቸው ግለሰቦች ናቸው። መቼም እነስዬ አብርሃና እነገብሩ አሥራት ወዘተ. . . የመሳሰሉ ግለሰቦች ከ18 ዓመት በፊት ዱዴ ያልነበራቸው፣ በዚህ 18 ዓመት እድሜ ውስጥ ሚሊዮኖች በሚራቡባት ኢትዮጵያ ውስጥ፣ በሃብታቸው ብዛት እንደፈረንጆቹ ሚሊየነሮች ባይሆንም ስማቸው ሲጠራ ብንስማ ወይ ጉድ! ከማለት በላይ ብንሄድ ሊያስገርም አይገባም። በጠባብ የጎጥ ድርጅት ጥላ ሥር ሆነው (የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት በማቋቋም) ትግራይን "ነፃ" እናወጣለን ብለው ከራሱ ከትግራይ ህዝብ እንኳ በዚህ በተባለው ትግል ውስጥ ስንቱ ሰው ረግፎበት እያለ ዛሬ "ነፃ" አውጥተንኃል ካሉት ህዝብ በላይ በኃብታቸው ብዛት ስማቸው ጎልቶ ሲጠራ ቢሰማ፥

### አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፤
### የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ።

በማለት የተቀኙትን የሀገራችንን የግፍ ሮሮ ማስታውሱ ሲያንስ ነው። የህዝባችን ድምፅ እንዲከበርና የሕዝባችን ድምፅ ደግሞ ሥርዓትን አበጅቶ ጉልበተኞችንና እብሪተኞችን ገና ከወዲሁ ሲያቆበቁቡ እምቢኝ እንዲል ካላበቃነው በቀር፣ የተንጠለጠለውን ዘረኛና ግፈኛ አገዛዝ በዝምታ አውጥተን ማውረድ እንደተቸገርነው ሁሉ፣ በሌላ ዙር መጥተው ሊገዙ ለሚቅነዘነዙት እብሪተኞችም ምንም ዋስትና የለንም እላችኋለሁ። ደግመን ደጋግመን የሕዝባችን ድምፅ ይከበር ብለን መጮህ ያለብን በጠመንጃ ለታጠረው የወንበዴው አገዛዝ ብቻ ሳይሆን፣ ከመጣ አምባገነን አገዛዝ ጋር በመጠጋት የሚጠግቡና የጠገቡ ቱጃሮችንም እንደሻቸው እንድይራገጡ ማገጃ መሣሪያችን የህዝባችን ድምፅ ተከብሮ ሥርዓት ሲያብጅልን ነው። እነስዬ አብርሃና መሰሎቹ ዛሬ ለበደሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ ጠይቁ ተብለው

በኢትዮጵያኖች ሲጠየቁ "ዛሬ የማወራርደው ሂሳብ የለኝም" ብሎ እስከመናገር ያበቃቸው ይህንን ስለሚያውቁ ነው፣ የዘረፉት ኃብትና ገና የሚቦጠቡጧት ኢትዮጵያ ስላለች እስካለን ድረስ ማንም ሊጠይቀን አይችልም ነው ዛቻቸው። ማንስ ነው የሚጠይቀን በማለት ዛሬም 80 ሚሊዮንን ህዝብ ንቀውና በእብሪት ተወጥረው ነው ። በእኛ በኩል ለእነ ስዬና ለአረናዎች ይቅርታ መጠየቅ አለባችሁ ስንል ጥያቄው ግልጽ ነው። ወያኔ ብለው ባበጁት ሥርዓታቸውና በጠመንጃቸው ጫፍ አጮልቀው እየተመለከቱ ኢምንት አድርገው ሲያዩት፣ ሲበድሉትና ቤት አልባ ሲያደርጉት የነበረውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ከመለስ ጋር ተጣልተን ወጣን ካሉ ዘንዳ ይህንን ህዝብ ስለማክበራቸው በይቅርታ ይግለፁለት ነው እየተባሉ ያሉት። ይህ ማለት የመጀመሪያው አክብሮት ሊሆን የሚችለው፣ በሠራነው ሥራ ተፀጽተናል በማለት በምንም ዓይነት ፖለቲካ ውስጥ ላለመሳተፍ እጃቸውን እንዲሰበስቡ የሚጠይቅ ነው። በሌላ አነጋገር - ከፖለቲካ ገለል (ሪዛይን) አድርጋችሁ አርፋችሁ ተቀመጡ የሚል እንጂ፣ ለፍርድ ቅረቡ ያለ የለም። ይቅርታ ጠይቁ ማለት ለፍርድ ቅረቡ ማለት አይደለም። በሕግ አግባብ የሚከናወንን የፍትህ ሂደት ከይቅርታ ጋር ማገናኘት ራሱ ተጨማሪ ሌላ ስህተት ነው። በተጨማሪም በሕዝብ የተቋቋመ መንግሥት ስለሌለ ይቅርታ የምንለው ለማን ነው በሚል እነ ስዬ ጥያቄውን ለማውገርገርና የነገሩን ውል ለማሳት መሞከር ራስን ማታለል ይሆን እንደሆን እንጂ መቼም ቢሆን መቼ ፍሬ ነገሩን ወይም ጥያቄውን ጨርሶ አይቀይረውም። ጥያቄው አሁንም ግልጽና የማያሻማ ነው። እነስዬ ሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት የገደሉት አገርንም ነው - ሰው ብቻ አይደለም። በዚህ ድርጊታቸውና በደላቸው ዛሬም ካልተፀፀቱ እንዳበዩ ናቸውና፣ ይህንን ያልበረደ ጥጋባቸውን እንዲያቀዘቅዙት ለኢትዮጵያ እነቆረቆራለን የምንል በሙሉ በአንድ ላይ ቆመን ጥግ ያዙ ልንላቸው ይገባል - ጥግ ያዙ አለቀ። የጠገቡት ሠርተው ሳይሆን ዘርፈው፣ ከሕግ በላይ ሆነው ነውና። ስለሆነም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ ለማለት ካልደፈሩ "ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አልያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል" ነውና ነገሩ ለራሳቸው ሲሉ ነው ሊያደርጉት የሚገደዱት።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

እንደ እውነቱ ከሆነ አሁን በ2002 ዓ.ም የሚደረገው ምርጫ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚማርክ ሆኖ አልተገኘም። ብዙም ያስጨነቀው መስሎ አይታይም። ይልቁንስ በጣም የተጨነቁትና የተጠበቡት እንደነኮማንደር ብርሃኑ ነጋና የመሳሰሉት ባለሃብቶች አገር ቤት በቤተሰቦቻቸው አማካኝት የሚያንቀሳቅሱትን ንብረታቸውን እዚህ ውጭ ሆነው በስማ በለው ከመቆጣጠር፣ አጠገቡ ቀረብ ብለው ምን ላይ እንደደረሰ መከታተል አጓጉቷቸዋል። ስለዚህ ከ"ምርጫው" ጋር በተያያዝ በየጊዜው የአቋም መገለባበጥ ቢያሳዩ የጮሌዎች ፖለቲካ ነውና አልተደነቅንም። ወያኔ ደግሞ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ወደደም ጠላ ወቅቱን እየጠበቀ ምርጫ የማድረግ ግዴታ አለበት። ዋናዋ ሸሪኩ አሜሪካም ሆነች፣ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ገንዘብ የሚያፈሱለት የምዕራብ አውሮፓ አገሮችም ወያኔ ምርጫውን እንዲያደርግ ያስገድዱታል። አለበለዚያ ወይ እንደ ሻዕቢያ ከመጀመሪያው ጀምሮ ምርጫ ሳያደርግ "ንጉሠ ነገሥት አፈወርቂ ዘ ባህረ ነጋሽ" መሆን ነው፣ ወይም ደግሞ በርካታ የአፍሪካ መሪዎች እንደሚቀልዱት ምርጫ እያለ የወዲ ዜናዊ ልጅ ብቅ በማለት አሸበል ገዳዬ ማለት አለበት ። የዘንድሮውን የወያኔ ምርጫ ለማጀብ ከታወቁት ውጭ በተጨማሪ ከአንድነት ኃይሎች እያፈነገጡ በመውጣት አለና እያሉ እጅ በማውጣት ቱስ ቱስ የሚሉ ጥቂት በረሮዎችም አልታጡም- እንዲያም ሆኖ ግን የጀርባ አጥንት ስለሌላቸው አቤቱታ አስገብተው ገና እየተጠኑ ነው - ሥራ ፈት እንዳትሉኝ እንጅ!!!

ለመሆኑ ለ2002 ምርጫ ያኮበኮቡ እነኝህ ኃይሎች እነማን ናቸው?
አብዛኛዎቹ አጃቢዎች በ1982 ዓ.ም ኢትዮ. አቆጣ፣ (1999 አውሮ፣አቆጣ.) በሎንዶን ታዛቢ ወይም ተሳታፊ በመሆንና በማጀብ ወያኔን "ኢሕአዴግ" አድረገው በስጦታ ያቀረቡልን ግለሰቦች ናቸው። ከፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ጀምሮ እስከ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ዓይነት ሰዎች፣ የምናውቀውን ወያኔ ለገላጋይ አስቸግረው "ኢሕአዴግ" ሆኗል ብለው ነገሩንና በዚያው ውስጥ ገብተው ደግሞ የወያኔ አማካሪና ደጋፊው ሆነው ተጠረነፉ። በዚህ በተጠረነፉበት የመንደር ድንኳን ውስጥ እንደታዘብነው ኢትዮጵያን ለማይወደው ወያኔ ደግሞ ያለ ልኩ ኢትዮጵያዊ ካባ አላበሱና እንዲንፈላሰስ ፈቅደው ንጣፍ ሆኑለት። ሁሉም "ምሁር" ነን ባዮች እነኝህ ግለሰቦች፣ በየጎጣቸው ተኮለኮሉና ድርጅት አቋቋምን ብለው አያታቸውን ሻዕቢያንም ሳይረሱ አጆሃ እያሉ አብረው ሲጦሩት ኖሩ። በለንደንና በአዲስ አበባው የሽግግር ጉባዔ ተብየ የተፈለፈሉት እነኝህ የጎጥ "ዴዴዎች" ከዋናው ወያኔ ጋር ሆነው ኢትዮጵያን ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከፊትና ከኋላ ሲንጧትና ሲጓትቷት ኖረው ከወያኔ በላይ ወያኔ ሆነው አጥር ግድግዳ በመሆን 18 ዓመት ወያኔን ገትረው አቆሙ። ጎምቱ ፕሮፌሰርም "ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ" እንደሚባለው ሎንዶን ላይ "ኢሕአዴግ ዴሞክራሲያው ግንባር" ነው ብለው ታዛቢነታቸውን ሠጥተው ምስክርነታቸውን ሰምተን ሳናብላላው ሳይውል ሳያድር ደግሞ የመሰከርኩለት ግንባር "ዴሞክራሲን" እያስለቀሰ ነው ብለው እንባ ጠባቂ ሆኛለሁ አሉንና "የሰብዓዊ መብት ተሟጓች ድርጅት" አቋቋምኩ ብለውን እርፍ። ሌላኛው ፕሮፌሰር ደግሞ ጥሎባቸው ማጋፈር ይወዳሉና አጋፋሪነቱን ወስደው ባርኔጣና ጭራቸውን እያኩነሰነሱ "ያላዋቂ ሳሚ" በሆነው "ሽምግልናቸው" የሕዝብ ብሶት ገንፍሎ በወጣ ቁጥርና አገር ቀውጢ ሲሆን እንደ እሣት አደጋ ሠራተኛ ውኃቸውን ይዘው ለማጥፋት ፊሽካ እየነፉ 18 ዓመት ከረሙ። ታዲያ እንዲህ በማድረግ የባጁት "ምሁሮቻችን" ያኔ ወያኔን ሞሻሽረው "ኢህአዴግ" ብለው የሠጡን ሰዎች ዛሬ ደግሞ በ2002 ዓ.ም ለሚደረገው ምርጫ ይዘታቸው ሳይቀየር የቅርጽ ለውጥ ብቻ አድርገው ታዲያሳ! ታውቁናላችሁ? እያሉን ነው። አይገርምም! በ1983 ዓ.ም (1991) የሎንደን ተዋንያን የነበሩት ወያኔ/ኢሕአዴጎች ዛሬ ደግሞ በ2002 ዓ.ም (2010) ምርጫ አረና/መድረክ በሚል ዘንቢል ተካተው ብቅ ብለዋል።እንታይ ጉዱ!! ሁሉም ደግሞ የጎጥ ማህበር ሆነው እያለ የስዬው "መድረክ" ሕብረ ብሄር አድርጎናል ብለው ያሳቁናል ሃ! ሃ! ሃ! ሃ! ግን ስም ከእነ አባት ቢባሉ <u>*ወያኔ*</u> ይሉና ፣ የአባት ስም ሲባሉ ደግሞ <u>*"ኢህአዴግ"*</u> በማለት የአያት ስም ከተባለ ደግሞ <u>*ሻዕቢያ*</u> ብለው እርፍ። ለነጮቹ ደግሞ ሲመቻቹ፣ ስም ከእነ አባት ሲባሉ <u>*አረና*</u> ይሉና የአባት ስም ተብለው ሲጠየቁ ደግሞ <u>*"መድርክ"*</u> በማለት! የአያትስ ሲባሉ <u>*"ኢሕአዴግ"*</u> ብለው ቁጭ። አዬ! ኢትዮጵያ! ስንቱን ጉድ ተሸከመሻል!

<u>በ1983 ዓ.ም (1991) በመዝገብ የተቀመጠው (ስም ከእነ አባት)</u>

ስም - ወያኔ
የአባት ስም - "ኢሕአዴግ"
የአያት ስም - ሻዕቢያ

<u>በ2002 ዓ.ም (2010) የተመዘገበው ደግሞ (ስም ከእነ አባት)</u>

ስም - አረና
የአባት ስም - መድረክ
የአያት ስም - ወያኔ/ኢሕአዴግ

ይህች ናት ጨዋታ አለ! ጥላሁን ገሠሠ!!! የጉድ አገር

በሉ ቸር እንሠንብት!

## የሕዝብ ድምፅ ይከበር! የታሠሩ የፓለቲካ እሰረኞች ይፈቱ!

## ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

February 21/2009